የአውሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ምክር ቤት
The Council of Europe and Africa Kinijit Support Groups

1 Crowndale Road London NW1 1TU UK Tel: +44 (0) 20 7168 9893 Email: euafkinijit@googlemail.com

## የተሰጠዉ ብይን፤ፍትህ ከሕዝብ እንጂ ከአምባገነኖች እንደማይገኝ ያረጋግጣል!!

ሰሞኑን በችሎት ላይ የሰነበተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት በመባል የሚታወቀዉ የወያኔ የይስሙላ ፍርድ ቤት የህሊና እስረኞች የሆኑት የቅንጅትና የሲቪክ ድርጅቶች መሪዎች በሀሰት የቀረበባቸዉን የዘር ማጥፋት፣ የሀገር ክህደትና ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል የመናድ ወንጀል ክስ አስመልቶ ጥፋተኞች ናቸው የሚል ብይን ሰጥቷል:: ብይኑን የኢትዮጵያ ሕዝብና ለሰብዊ መብት መከበር የቆመዉ የዓለም-አቀፍ ህብረተሰብ በመገረምና በቁጭት ሰምቶታል:: የተሰጠዉ ብይን ከአንድ ዓመት በላይ በፍትህ ስም ሲከሄድ የቆየው አሳዛኝ ድራማ ወደ መጠናቀቁ መቃራቡንና መጋረጃዉ ለመጣል ዝግጁ መሆኑን አብስሯል:: ይህ በዘረኛ ውና በፋሺስቱ መለስ ዜናዊ ተደርሶ፣ ሕዝብ «የከድሬ ማምረቻ» እያለ ከሚጠራውና የሥርዓቱ ታማኝ አገልጋዮች ማረቂያ ከሆነው ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በወጡ አድርባይ ዳኖች ተዋናይነትና በገንዘብ በተገዙ ሆድ-አደር ምስክሮች አጃቢነት የተከወነው አሳፋሪ ድራማ፤የሚሊኒየሙ ታላቅ «የፍትህ ቅሌት» ተብሎ በታሪክ አምድ እንደሚመዘገብ የሚያጠራጥር አይሆንም::

ይህ ፍርደ-ገምድል ብይን የኢትዮጵያን ሕዝብ ማስቆጣቱና ማሳዘኑ ባይቀርም ያልተጠበቀ ግን አልነበረም:: አጠቃላይ የክሱ አመሰራረትና የፍርድ ሂደት ለተከታተለና የወያኔን ዕውነተኛ ባህርይና ታሪክ ጠንቅቆ ለሚያውቀዉ ዜጋና ሌላ ተመልከች የሚያስደንቅም አይሆነም:: ከሁሉም በላይ የተዛበዉ ፍትህ ሰለባ የሆኑትና በማያወላዉል የአቋም ጽናታቸዉ የሚታወቁት የቅንጅት መሪዎችም ጉዳዩን ዋጋ ሰጥተዉት ይዘዉት ከቆዩት እምነትና አቋም ትንሽ ፈቀቅ ያደርጋቸዋል ተብሎ አይጠበቅም:: ብይኑ ያረጋገጠዉ ነገር ቢኖር የወያኔ አገዛዝ ለዴሞክራሲና ለሰው ልጆች መብት መከበር ያልቆመ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ንቅትና ጥላቻ፣ ደንታቢስ ለበቀል የቆመ አምባገነናዊ ሥርዓት መሆኑን ነው:: ብይኑ በግልጽ ያረጋገጠዉ ሌላዉ ሐቅ በወያኔ አገዛዝ የፍርድ ሥርዓቱና የዳኝነት ሙያ ምን ያህል የተዋረደ መሆኑን፣ ዳኛ ተብየዎቹ ምን ያህል በወረደ የሙያ ሥነ-ምግባርና የሞራል ዝቅጠት ዉስጥ ተዘፍቀዉ እንደሚገኙና፤ በዚህ ሥርዓት ፍርድና ፍትህ የፓለቲከ መሣሪያ መሆናቸዉን ነዉ::

የአንድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋንኛ መመዘኛዎች የተለያዩ አመለካከቶችና አማራጮች መስተናገድ መቻል፣ ሕዝብ የራሱን መሪዎች የሚመርጥበትና የህግ የበላይት የተረጋገጠት ሥርዓት መኖር ናቸው:: የቅንጅት መሪዎች ሰላማዊና ሕጋዊ የፓለቲካ ትግል አካሂደው የሕዝብን ሙሉ አመኔታና ፍቅር አግኝተው የተመረጡ የሕዝብ መሪዎች እንጂ ሽብርተኛና ወንጀለኛ አለመሆናቸዉ በማንም ዘንድ የሚታወቅ ዴሞክራቶች መሆናቸዉም የአደባባይ ምስጢር ነዉ:: ዓለም የሚያወቀዉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተሸራረፈ ነጻነትና መብት፣ለአንድነት፣ለሰላምና ለብሄራዊ እርቅ የቆሙ፣ያስተማሩ የሰላም መልዕክተኞች መሆናቸዉን ነዉ:: የቅንጅት መሪዎች የዘረኝነትን እግረ-ሙቅ በመስበር ሕዝብ ያቀራረቡ፣የኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት እንደገና ያደሱ ትውልድ በአርአያነት እየጠቀሰ ሲኮራባቸው የሚኖር የዘመኑ ጀግኖችና አርበኞች ናቸው:: የቅንጅት መሪዎች የሚዳኙት በሕዝብ፣በትውልድና በታሪክ እንጂ፣ ከሥልጣን ለሚገኝ ጥቅም ላበደ ከሃዲ ቡድን አይደለም:: ማንንም ጤነኛ አእምሮ ያለዉ ሰዉ «ከእባብ እንቁላል እርግብ ይፈለፈላል» ብሎ እንደማይጠበቅ ሁሉ **የቅንጅት መሪዎችና የሰብአዊ መብት ታጋዮች ፍትህን ከኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ** የዘረኝነት በሽታ ከተጠናወተው ወያኔ ፍትህ እናገኛለን ብለዉ አይጠብቁም::

ቅንጅት የሰላምና የእርቅ ሃይል ነው:: በየትኛዉም ቦታና ጊዜ አመጽን የፓለቲከ ችግር መፍቻ አድርጎ ተመልክቶ አያውቅም:: በየትኛዉም መለኪያ ቅንጅት በዘረኝነት አይታማም:: ቅንጅት ትናንትም ሆነ ዛሬ የሀገሪቱ ችግሮች ሁሉንም ወገን ባከተተ ሁኔታ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ በውይይት መፈታት አለባቸው ብሎ ያምናል:: የሠራዉ ወንጃልም ይህና ይህ ብቻ ነዉ:: በመሆኑም በዘር ማጥፋት ወንጀልም ሆነ በነዉጠኛነት መከሰስ የሚገባቸዉ የሰላምና የብሄራዊ እርቅ ሐዋርያ የሆኑት የቅንጅት መሪዎች ሳይሆኑ ሕዝብን በአጥንትና በጉልጥምት እየለያየ፣ በክልልና በጎጥ እየሸነሸነ፣ በከፋፍለህ ግዛዉ ፖሊሲዉ እያተራመሰ፤ ሰላማዊ ዜጎችን የፈጀና ያፋጀ፣ መንግሰታዊ ሽብርን የሚያራምደዉ ራሱ ወያኔ ነው:: ነፍጠኛና ትምክህተኛ እያለ በሚጠራዉ ወገን ላይ በበደኖ፣በአሩሲ፣ በደቡብ ሸዋና በወለጋ የፈጸመዉ ግፍ የሚረሳ አይደለም:: እርጉዞች ሆዳቸው በሳንጃ እንዲዘነጠል፣ አቅመ ደከማ አረጋዉያንና ሕጻናት ቤት ተዘግቶባቸው

እንዲቃጠሉ፤ምዕመናን ወደ ገደል እንዲወረወሩና እንዲታረዱ ያስደረገዉ ወያኔ ስለመሆኑ ያልደረቀዉ ደም አሁንም ይጮሃል። በጋምቤላ፣በአዲስ አበባና በሌሎችም ቦታዎች ሕዝብን በጅምላ የጨፈጨፈ፤ በዴዴሳ፣ በብር ሸለቆ፣በደንቆሮ ዋሻ፣በዝዋይና በሌሎችም የማጎሪያ ጣቢያዎች የሕዝብ ልጆችን ያሰቃየና የገረፈ ብሎም በዘር ማጥፋትና በጦር ወንጀለኝነት የሚጠየቀዉ ዘረኛ ውና ፋሺስቱ ወያኔ እንጂ የቅንጅት መሪዎቹ አይደሉም። ነገሩ አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ ካልሆነ በስተቀር።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገሩ ላይ የመከራ ሕይወት እንዲገፋ ተፈርዶበታል። ብዙ የተወራለት ልማትና ዕድገት ከምጽዋት መለመኛነት ያለፈ አይደለም። የፕሮፓጋንዳ ማፈሰሻ አሸንዳዉ ወያኔ በኢትዮጵያ ዉስጥ ስላመጣው ዴሞክራሲና ስላስመዘገበው የልማት ግስጋሴ ቢደሰኩርም፣ የመከራ ሕይወት መግፋት ዕጣ ፈንታዉ የሆነው ሕዝባችን አንጀቱን አስሮ እፍኝ የማይሞሉ የሥርዓቱ ጋሻ-ጃግሬዎች የሚመሩተን የአስረሽ ምቺው ቅምጥል ኑሮ በአርምሞ ከመመልከት ዉጭ የተረፈዉ ነገር የለም። ወያኔና አጫፋሪዎቹ የሆኑ ጥቂት የጎሳ አበጋዞች ሰንጋ ጥለው ጮማ እየቆረጡ ስላገሱ፣ብርጭቆ እያጋጩ ውስኪ እንደ ውሃ ስላፈሰሱ፣ ማኛ ከሰርገኛ ስላማረጡ፣ ከበሮና ድቤ እየደለቁ «አሸወይና» ስለዘፈኑ የሰፊዉ ሕዘብ እንባ ደረቀ፣ኑሮው ተሻሻለ ማለት አይደለም። ሰፊው ሕዝብ ዛሬም ሽሮና እፍኝ ቆሎ አሮበት፤ አንጀቱን አስሮ የበይ ተመልካች በመሆን ግማሹ ለልመና ሲዳረግ ሌላው በረሃብና በሽታ በመርገፍ ላይ ይገኛል።

ኢትዬጵያ ከምን ጊዜውም በላይ ጠመንጃ ነካሽ በሆነ ሃይል መዳፍ ሥር መዉደቋ የሚያጠያይቅ አይደለም። ታሪክና ክብርዋ ከመዋረዱም በላይ በደም በባህልና በቋንቋ የተሳሰረውና ለዘመናት ተከባብሮ አብሮ በሰላም የኖረው ሕዝብ በጎሳ፣በሃይማኖት፣በጎጥና በቆጥ ተከፋፍሎ እርስ በርሱ እንዳይተማመን የሚደረገው ጥረት በሰፊው ቀጥሏል። በመሆኑም ወቅቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለት አማራጭ አቅርቦለታል። አንደኛዉ አማራጭ ለራሱና ለቤተሰቡ በአጠቃላይም ለሀገራዊ መብቱ፣ ነጻነቱና ክብሩ ሲል አንድነቱን አጠንክሮና ሃይሉን አቀናጅቶ፣ ብርቅየዎቹ የቅንጅት መሪዎች ያሳዩትን የዓላማ ጽናትና ስብዕና ተላብሶ፣ መታገልና ራሱን ነጻ ማውጣት ነዉ። ሁለተኛዉ አማራጭ ደግሞ እስራትን፣ ግድያን፣ ስደትንና ጭቆናን ተቀብሎ የባሪያ ባሪያ ሆኖ በተዋራጅነት የሰቆቃ ሕይወት መኖር ነዉ። ባርነትንና ተዋራጅነትን ተቀብሎ እየተረገጡ መገዛት ደግሞ የጀግናዉ ኢትዮጵያ ሕዝብ መለያ ታሪክና ባህል አይደለም። ስለሆነም ወያኔ ስልጣን ላይ ለመቆየት ምንም ዓይነት ወንጀል ለመፈጸም ወደኋላ እንደማይል ከመቸውም ጊዜ በላይ ግልጽ በሆነበት በአሁኑ ወቅት አባቶቻችን ያወረሱንን የሀገርና የወገን ፍቅር ሰንቀን በምንከፍለዉ ክቡር መስዕትነት ነጻነታችንን ማስመለስ ቅድሚያ ተግባራችን መሆን ይኖርበታል።

ፍትህ፤ነጻነትና ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ዓርብ፤ አፕሪል 6 ቀን 2007

›